# የቤተ ክርስቲያን ማሳሰቢያ

### የአርብ ፕሮግራም

በአርብ ፕሮግራም እግዚአብሔር ግሩም የጸሎትና የትምህርት ጊዜ እየሰጠን ነው። በዚህ የጸሎት ፕሮግራም ላይ በመገኘት በጸሎትና ቃሉን በመማር እንድንተጋ ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። እንዲጸለይላችሁ የምትፈልጉ ወገኖችም መሪዎችን ማነጋገር ትችላላችሁ። ጌታ ይባርካችሁ።

### የልጆች አግልግሎት ቀን

በOctober 27 በሚኖረው የሕሁድ አገልግሎት ልጆቻችን አዋቂዎችን የሚያገለግሉበት እለት ነው። በዚህ እለት ስለሚኖረው ፕሮግራም እየጸለይን እንድንቆይ እናሳስባለን። የተለየ ግሩም ግዜ ስለሚኖረን በዚህ ፕሮግራም ሁላችንም እንድንካፍለ እናበረታታለን።

### እርስ በርስ እንተያይ

ባለፈው ሳምንት የጀምርነውን ለሌሎች ወገኖቻችን የመደወል እና እርስ-በእርስ የመጠያየቁን ነገር አጥብቀን እንድቀጥል ቤተ ክርስቲያን ታሳስባለች። በዚህ አገልግሎት እየተጋችሁ ያላችሁ ወገኖች እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

"ወደ ውጭም አውጥቶ፡- ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
እነርሱም፡- በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።" (ሐዋ. 16፡ 30-31)



- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?


ሽማግሌዎችን ለማግኘት፡-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)


**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

---

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

"እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ" ሉቃስ 2፡10

# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!




"… መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ…"
(ሐዋ. 1:8)


Chicago Yemsrach Evangelical Church
4455 N. Seeley Avenue
Chicago, IL 60625


መደበኛ ፕሮግራሞች
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

**October 13, 2019** | **ጥቅምት 2፣ 2012 ዓ.ም.**

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

**ጸሎት** ............................ ወንድም ብርሃኑ አንበሴ

**አምልኮ**.......................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

**ፕሮግራም መሪ** ............. ወንድም ሲሳይ መሸሻ

**ቃል** ................................ ፓስተር በፍቃዱ አተመ

**ማጠቃለያ** ...................... ፕሮግራም መሪ

### <u>የሳምንቱ ጥቅስ</u>

“እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።”
(2 ጢሞ. 1:7)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | 5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640 |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | 7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645 |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | 7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660 |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | 7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645 |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | 7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631 |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | 9107 Laramie St. Skokie, IL 60077 |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | 5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640 |
| | | |

# መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ረድኤቱ ካሳ

### መንፈስ ቅዱስ የኃይል መንፈስ።

*“... መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ...” (ሐዋ. 1:8)*

መንፈስ ቅዱስ የኃይል መንፈስ ስለሆነ በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ ኃይልን እንቀበላለን። መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ኃይል በተለያየ መንገድ የሚገለጥ ነው። በላይ በሰፈረው ክፍል ቃሉ መንፈስ ቅዱስ በኛ ላይ ሲወርድ ኃይልን እንደምንቀበል ይናገራል። አያይዞም ደግሞ ይህ የሚሰጠን ኃይል ምስክሮች እንደሚያደርገን ይናገራል። መንፈስ ቅዱስ ከተሞላን በኋላ የጌታ ምስክሮች እንደምንሆን ይናገራል። ሁለት ነገሮች በዚህ ክፍል እንመለከታለን። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስን ስንቀበል አለምንም ቅድመ ሁኔታ የጌታ ምስክሮች እንሆናለን። መንፈስ ቅዱስን ተቀብለን ስለ ጌታ ምስክሮች አለመሆን አንችልም። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ስለ ጌታ የሚመሰክር ስለሆነ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ጌታ ሲናገር “ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ” ብሎናል። (ዮሐ. 15፡ 26-27) መንፈስ ቅዱስ ስለ ጌታ የሚመሰክር በመሆኑ እኛም ደግሞ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ስለ ጌታ አብረን እንመሰክራለን። ሁለተኛው ከክፍሉ የምናስተውለው ሃሳብ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ኃይል እያደገና እየሰፋ የሚሄድ እንደሆነ እናያለን። ሐዋሪያቱ እንደመጣላቸው ቃል ምስክርነታቸው ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በይሁዳና በሰማሪያ ዘልቆ እስከ ምድር ዳር እንደ ሄደ ሁሉ እኛም በተሰጠን በመንፈስ ቅዱስ ምስክርነታችን እያደገና እየበዛ የሚሄድ ይሆናል። እንግዲህ የምናስተውለው የመጀመሪያው ነጥብ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ኃይል ምስክሮች እንደሚያደርገን ነው።

መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠን ኃይል በተግዳሮት ፊት በጽናት ለመቆም የሚያስችለን ነው። በሐዋሪያት ስራ ምዕራፍ አራት ላይ ስናነብ ጴጥሮስና ዮሐንስ በቤተ መቅደስ ደጃፍ የነበረውን ከመወለዱ ጀምሮ አንካሳ የነበረውን ሰው በጌታ በኢየሱስ ስም ከፈወሱት በኋላ በወቅቱ የነበሩት የኃይማኖት መሪዎች ተነሱባቸው። እንዲያውም በጌታ በኢየሱስ ስም ዳግመኛ እንዳይናገሩ በከፍተኛ ዛቻ አስፈራርተው ለቀቋቸው። ይህንንም ጉዳይ ይዘው ቅዱሳን በአንድ ልብ ወደ ጌታ በጸሎት ቀረቡ። ጸልየው ሲጨርሱ “ተሰብስበው የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ” (ሐዋ. 4:31)። መንፈስ ቅዱስን እንደገና ከተሞሉ በኋላ ሐዋሪያቱ ቃሉን በግልጽ ተናገሩ። ይህ የሚያሳየን ከገጠማቸው ተግዳሮት በኋላ በጸሎት መንፈስ ቅዱስን ተሞልተው እንደገና ቃሉን በኃይል እንደ ሰበኩ ነው። “በግልጽ ተናገሩ” የሚለው ኃሳብ የሚያሳየው ቃሉን ያለፍርሃት፣ በድፍረት መናገራቸውን ነው። መንፈስ ቅዱስ ቃሉን በስልጣንና በድፍረት እንድንናገር ኃይልን ይሰጠናል። ቃሉን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስንናገር የሚቋቋመን አይኖርም። ለዚህ ነው ስለ እስጢፋኖስ ቃሉ ሲመሰክር “ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም” የሚለን። (ሐዋ. 6:10) ጌታም እንደሰተን የተስፋ ቃል በመንፈስ ቅዱስ ስንሞላ “ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ” እንቀበላለን። (ሉቃ. 21:15)

ወገኖቼ፡- መንፈስ ቅዱስ የኃይል መንፈስ ነው። ለክርስቶስ ምስክሮች እንድሆን ኃይል ይሰጠናል፤ ደግሞም በተግዳሮት ፊት በጽናት የሚያቆም ኃይል የሰጠናል።